# አዲስ የተዘጋጀው ረቂቅ የኢንቨስትመንት አዋጅ ማብራሪያ

## ክፍል አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የማብራሪያው ዓላማ

ይህ ማብራሪያ በሥራ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ሕግ (የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 እና የኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር 270/2005 (እንደተሻሻሉ)) የሚተካ አዲስ ሕግ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተዘጋጅቶ እና በሚመለከታቸው የመንግሥት እና የግሉ ዘርፍ አካላት በተሰጠ አስተያየት መሠረት ዳብሮ የተዘጋጀውን ረቂቅ የኢንቨስትመንት አዋጅ ይመለከታል፡፡ የማብራሪያው ዓላማ በረቂቅ አዋጁ ውስጥ የተካተቱ ድንጋጌዎች የተካተቱበትን ዓላማ፣ ምክንያት እና አመክንዮ እንዲሁም ተፈጻሚ እንዲሆኑ የታሰቡበትን ሁኔታ እና አግባብ በማመልከት የፖሊሲ ወሳኞች እና ሕግ አውጭዎች ተገቢውን ውሳኔ እንዲወስኑ ማስቻል፣ ሕጉ ከጸደቀ በኋላም ድንጋጌዎቹ በሕጉ ውስጥ ያላቸውን ይዘት እና ቅርጽ በጠበቀ መልኩ እንዲፈጸሙ ማስቻል ነው፡፡

### 1.2 የኢንቨስትመንት ሕጉን ማሻሻል ያስፈለገበት ምክንያት

በኢትዮጵያ የነጻ-ገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መተግበር ከጀመረበት 1984 ዓ.ም. ጀምሮ አሁን በሥራ ላይ ያለውን አዋጅ ቁጥር 769/2004 ጨምሮ በ 1984፣ 1988፣ 1994 እና 2004 ዓ.ም. መሠረታዊ ዓላማቸው ኢንቨስትመንትን መሳብ፣ ማበረታታት፣ ማስተዳደር እና መጠበቅ የሆነ የኢንቨስትመንት አዋጆች እንዲሁም ደንቦች ወጥተዋል፡፡ እያንዳንዱ አዋጅ እና ደንብ የተዘጋጀው በጊዜው የነበረውን የአገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እና የልማት ግቦች ያማከለ የኢንቨስትመንት ፖሊሲን መሠረት በማድረግ ሲሆን የአዋጆቹ እና ደንቦቹ ይዘት የተዋቀረውም አገሪቱ በኢንቨስትመንት ሥራዎች ለማሳካት ያቀደቻቸውን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎች ዕውን ለማድረግ እንደሚያስችሉ በታመነባቸው ጉዳዮች ነው፡፡ በዚህም መሠረት፤ በሥራ ላይ ያሉትን ጨምሮ ከዚህ በፊት ወጥተው የነበሩ አዋጆች እና ደንቦች የአገር ውስጥ እና የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን እያስተናገደ የሚገኝ የኢንቨስትመንት የሕግ ማዕቀፍ እና ከባቢ ለመገንባት አስችለዋል፡፡ ይህን የኢንቨስትመንት የሕግ ማዕቀፍ በተለያዩ ምክንያቶች በየጊዜው ከሚከሰቱ ለውጦች ጋር እንዲጣጣም ማድረግ ቀልጣፋ እና ተወዳዳሪ የኢንቨስትመት ከባቢ ለመገንባት አስፈላጊ ነው፡፡

በሥራ ላይ ያለውን የኢንቨስትመንት ሕግ ለማሻሻል ምክንያት ከሆኑ ጉዳዮች መካከል ሕጉ በአገሪቱ በአጠቃላይ ጉዳዮች በተለይ ደግሞ በኢኮኖሚው ዘርፍ እየተካሄዱ ካሉ ለውጦች ጋር እንዲናበብ ማድረግ፣ የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች በግሉ ዘርፍ ሊሳተፉ የሚችሉባቸውን

የኢንቨስትመንት ሥራዎች በመከለስ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚ ዕድገት እና ተወዳዳሪነት፣ በሥራ ፈጠራ፣ እንዲሁም በቴክኖሎጂ እና ክህሎት ሽግግር ላይ ያለውን ሚና ማሳደግ፣ የተጠቃለለ የሕግ ሰነድ በመጠቀም (በተለያዩ የማሻሻያ ሕጎች የወጡትን ጉዳዮች በመሰብሰብ) የኢንቨስትመንት አስተዳደር እና ቁጥጥር ሥርዓቱን ማዘመን፣ የኢንቨስትመንት ማነቆ ለሆኑ ጉዳዮች መፍትሔ በመስጠት የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር ማድረግ፣ እንዲሁም ግልጽ እና ውጤታማ የባለሀብቶች ቅሬታ የሚስተናገድበት ሥርዓት ማበጀት ማስፈለጉ ዋነኞቹ ናቸው። ስለሆነም፤ በዚህ ሰነድ በአጭሩ የተብራራው ረቂቅ የኢንቨስትመንት አዋጅ የተረቀቀው እነዚህን ለማሻሻያው ምክንያት የሆኑትን እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን መሠረት በማድረግ ነው።

## ክፍል ሁለት

## ረቂቅ የኢንቨስትመንት አዋጁ ያካተታቸው መሠረታዊ ማሻሻያዎች

### 2.1 አጠቃላይ የአቀራረብ እና የይዘት ለውጥ

በሥራ ላይ ያለውን ጨምሮ የቀድሞዎቹ የኢንቨስትመንት አዋጆች በኢንቨስትመንት ሕጉ የሚደነገጉ ሁሉንም ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ መሠረታዊ መርሆች እንዲሁም አብዛኞቹን የመርሆቹ ማስፈጸሚያ ድንጋጌዎች የሚዘረዝሩ ነበሩ። ይህ አቀራረብ መሠረታዊ መርሆቹን ከዝርዝሮቹ በቀላሉ ለይቶ ለመረዳት እንዲሁም በየጊዜው መሻሻል የሚያስፈልጋቸውን ዝርዝር ድንጋጌዎች በቀላሉ ለማሻሻል የማያስችል ስለነበር ለዚህ መፍትሔ እንዲሆን ረቂቅ አዋጁ መሠረታዊ መርሆችን እና መሠረታዊ መብት እና ግዴታ የሚያቋቁሙ ድንጋጌዎችን ብቻ እንዲይዝ፤ በአዋጁ መሠረት የሚወጣው ረቂቅ ደንብ ደግሞ የመሠረታዊ መርሆቹ እንዲሁም መብት እና ግዴታዎቹ ማስፈጸሚያ ዝርዝር ድንጋጌዎችን እንዲይዝ ተደርገው ተቀርጸዋል። በተጨማሪም፤ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ወደፊት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የገንዘብ ሚኒስቴር በሚረቀቅ ራሱን በቻለ ሌላ ሕግ (ደንብ ወይም አዋጅ) የሚወሰኑ በመሆኑ ረቂቅ አዋጁም ሆነ አዋጁን መሠረት የሚያደርግ ደንብ ለተመረጡ የኢንቨስትመንት መስኮች ማበረታቻ የሚፈቅድ መርህ ከማስቀመጥ ውጪ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ድንጋጌዎችን አያካትትም።

ይዘትን በተመለከተ፤ ረቂቅ የኢንቨስትመንት አዋጁ ሥራ ላይ ባለው የኢንቨስትመንት ሕጉ የተደነገጉ ጉዳዮችን ይበልጥ ውጤታማ እንደሚያደርጉ የታመነባቸው ማሻሻያዎችን ከማድረጉም በተጨማሪ ሌሎች አዳዲስ ጉዳዮችን ወይም አሠራሮችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችም አካቷል። ከነዚህም መካከል በሥራ ላይ ያለውን የውጭ ባለሀብቶች ሊሰማሩ የሚችሉባቸው የኢንቨስትመንት መስኮች ዝርዝር (positive list) ለውጭ ባለሀብቶች ዝግ በተደረጉ የኢንቨስትመንት መስኮች (negative list) የሚለውጥ፣ የኢንፎርሜሽን መገናኛ ቴክኖሎጂ አውታሮችን በመጠቀም የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና ሌሎች አገልግሎቶች ጥያቄዎች ማስተናገድ የሚያስችል፣

የኢንቨስትመንት ቪዛ እንዲሁም ለውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሥርዓት የሚመለከት ግልጽ እና አስቻይ መርሆች የሚያስቀምጡ፣ የአንድ መስኮት አገልግሎቶችን የሚያጠናክር እንዲሁም ወደ ክልሎች እንዲወርዱ የሚያስችል፣ አገራዊ እንድምታ ያላቸውን የኢንቨስትመንት ተግዳሮቶች በከፍተኛ የፌደራል መንግሥት እና የክልል መንግሥት አካላት ደረጃ መፍትሔ ለመስጠት የሚችል አካል የሚያቋቁም፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ስለሚችልበት ሕጋዊ አግባብ፣ በኮሚሽኑ የሚተላለፉ እና ከኮሚሽኑ ውጪ ያሉ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት የሚወስኗቸው ውሳኔዎች ላይ በባለሀብቶች ቅሬታ የሚቀርብበትን አግባብ የሚወስኑ ድንጋጌዎች ይገኙበታል።

## 2.2 የተሻሻለው ረቂቅ ኢንቨስትመንት አዋጅ ይዘት

ከላይ እንደተመለከተው፤ ይህ ማብራሪያ የሚያተኩረው መሠረታዊ የሀሳብ ወይም የይዘት ለውጥ የተደረገባቸው የአዋጁ እና የደንቡ ድንጋጌዎች ላይ ብቻ ነው። ረቂቅ አዋጁ በጠቅላላው 57 አንቀጾች ያሏቸው አስር ክፍሎች ያሉት ሲሆን ተያያዥነት ያላቸው በመሆኑ በአንድ ላይ ከታዩት የረቂቅ አዋጁ መግቢያ እና የክፍል ሁለት ድንጋጌ (የኢንቨስትመንት ዓላማዎች) በስተቀር ለአቀራረብ እንዲያመች ማብራሪያው እያንዳንዱ ለውጥ የተደረገበት ክፍል ውስጥ የተካተቱ የማሻሻያ ድንጋጌዎችን በአዋጁ በተቀመጡበት ቅደም-ተከተል ይመለከታል።

### 2.2.1 የረቂቅ አዋጁ መግቢያ እና ክፍል ሁለት - የኢንቨስትመንት ዓላማዎች

የረቂቅ አዋጁ መግቢያ (preamble) እና በክፍል ሁለት ሥር የአንቀጽ 5 ድንጋጌ አዲስ የኢንቨስትመንት ሕግ ያስፈለገበትን ምክንያት እንዲሁም ከኢንቨስትመንት ሥራዎች የሚጠበቀውን አገራዊ ጥቅም ያመለክታሉ። ኢንቨስትመንት የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የቴክኖሎጂ፣ ዕውቀት እና ክህሎት ሽግግር፣ የወጭ ምርቶችን በማሳደግ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን የማሳደግ፣ የአገሪቱን የተፈጥሮ፣ የባህል እና ሌሎች ሀብቶች ጥቅም ላይ የማዋል፣ የውጭ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርቶች በመተካት የውጭ ምንዛሪን የማዳን እና የመሳሰሉት ዝርዝር ዓላማዎች ኖሮት ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ልማት የማምጣት ዋና ዓላማ ያለው ስለመሆኑ በሥራ ላይ ያለው ሕግም ያመለክታል። እነኝህ ዝርዝር ዓላማዎች የበለጠ ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት ዋና ዋና አምራች እና አስቻይ የልማት ዘርፎች ላይ ልዩ ትኩረት ያደረገ ኢንቨስትመንት ሲኖር እንዲሁም በተለያዩ የልማት ዘርፎች መካከል ቀጣይነት ያለው እና ተመጋጋቢ ትስስር ሲረጋገጥ መሆኑ ስለታመነ የረቂቅ አዋጁ ዝግጅት እና ዓላማ እነኝህን ጉዳዮች ታሳቢ ያደረገ ነው።

2.2.2 **ክፍል አንድ፡ ጠቅላላ**

- <u>አንቀጽ 2 - ትርጓሜ</u>፡ በዚህ አንቀጽ ሥር በረቂቅ አዋጁ እና ደንቡ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የተለያዩ ቃላቶች የሚኖራቸው የሕግ ወይም የሌላ ሙያ ትርጉም ተመልክቷል፡፡ ከነዚህም መካከል ከዚህ በታች የተመለከቱት ላይ የሚከተለው ማሻሻያ ተደርጓል፡፡
  - ✓ አንቀጽ 2/1/፦ ለ"ኢንቨስትመንት" በተሰጠው ትርጓሜ አዲስ ድርጅትን ለማቋቋም ወይም ነባር ድርጅትን ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል ከሚደረግ በተጨማሪ ነባር ድርጅትን በከፊል (የተወሰነ አክስዮን ወይም ድርሻ) ወይም በሙሉ ለመግዛት በዓይነት ወይም በገንዘብ የሚደረግ ወጪንም የሚጨምር ስለመሆኑ በግልጽ ተቀምጧል፡፡
  - ✓ አንቀጽ 2/3/፦ በአዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 2/3/ ለ "ካፒታል" በተሰጠው ትርጓሜ ከሌሎች ንብረቶች በተጨማሪ "የፓተንት" መብት ካፒታል እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ ሆኖም፤ የፓተንት መብት ብቻ መገለጹ ሌሎች አእምሯዊ ንብረቶች ካፒታል ናቸው አይደሉም የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል በመሆኑ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት እውቅና የተሰጠው አእምሯዊ ንብረት በሙሉ በትርጓሜው እንዲሸፈን ለማድረግ "የፓተንት መብት" በ "የአእምሯዊ ንብረት መብት" ተተክቷል፡፡
  - ✓ አንቀጽ 2/5/፦ ለ "ባለሀብት" የሚሰጠው ትርጓሜ በኢንቨስትመንት ላይ ሊሰማሩ ለሚችሉ ለተለያዩ ሰዎች ወይም አካላት የተከለሉ ወይም ክፍት የተደረጉ የኢንቨስትመንት መስኮች ማንነት ላይ የሚመሠረት ነው፡፡ በሥራ ላይ ያለው የኢንቨስትመንት ሕግ መንግሥትን ጨምሮ ለኢትዮጵያውያን ብቻ የከለላቸው መስኮችን ስለሚደነግግ ባለሀብቶችን "ኢትዮጵያዊ ባለሀብት"፣ "የአገር ውስጥ ባለሀብት" እና "የውጭ ባለሀብት" በሚል በሦስት ምድቦች ያስቀምጣል፡፡ ረቂቅ የኢንቨስትመንት ሕጉ በሥራ ላይ ካለው አዋጅ በተለየ ሁለት የ"ባለሀብት" መደቦች (categories) ብቻ ይኖሩታል፡፡ አንደኛው ኢትዮጵያውያንን፣ መንግሥትን እንዲሁም ኢንቨስትመንትን በተመለከተ እንደ ኢትዮጵያውያን የሚቆጠሩ ትውልደ-ኢትዮጵያውያንን እና ሌሎች በዓለም አቀፍ ስምምነት ተመሳሳይ መብት ያገኙ የውጭ ዜጎችን የሚያካትተው "የአገር ውስጥ ባለሀብት" መደብ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የውጭ ዜጎችን ብቻ የሚመለከተው "የውጭ ባለሀብት" መደብ ነው፡፡ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች መደብን በተመለከተ፤ ከላይ ከተመለከቱት በተጨማሪ ኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ ነዋሪ በመሆናቸው በቀደምት ሕግጋት እንደ የአገር ውስጥ ባለሀብት ተቆጥረው የነበሩ ሆኖም አዋጅ ቁጥር 769/2004 ኢትዮጵያ ውስጥ ቋሚ ነዋሪ መሆን ለውጭ ዜጎች የአገር ውስጥ ባለሀብት የመሆን መብትን በማስቀረቱ የአገር ውስጥ ባለሀብት መደባቸው ላይ ጥያቄ ተፈጥሮባቸው የነበሩ የውጭ ዜጎችን እና ተወላጆቻቸውንም እንዲያካትት ተደርጓል፡፡ ሆኖም፤ እነዚህ የውጭ ዜጎች እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት የሚቆጠሩት ከዚህ ቀደም

ያቋቋሚቸው እና አሁንም በሥራ ላይ ያሉ ድርጅቶቻቸውን ወይም ኢንቨስትመንቶቻቸውን በተመለከተ ብቻ ይሆናል፡፡

✓ አንቀጽ 2/15/፦ የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድሮች የኢንቨስትመንት ጉባዔ “ጉባዔ” ለሚል ቃል ትርጓሜ ተቀምጧል (የዚህ አካል ምንነት እና ኃላፊነት የአዋጁን ክፍል ስምንት በሚመለከተው ማብራሪያ ተካቷል)፡፡

- <u>አንቀጽ 3 - የተፈጻሚነት ወሰን</u>፡

ከሌሎች የኢንቨስትመንት ሥራዎች የተለየ ባህርይ ያላቸው በመሆኑ የተለየ የሕግ ማዕቀፍ እና አስተዳደር የሚያስፈልጋቸው መሆኑ ታምኖበት አሁን በሥራ ላይ ካለው የኢንቨስትመንት አዋጅ የተፈጻሚነት ወሰን ውጪ የተደረጉት በማዕድን እና ነዳጅ መስክ የሚደረጉ የፍለጋ፣ የምርመራ እና የማምረት ሥራዎች አስተዳደር ለተሻለ ውጤት ወደፊትም ራሱን በቻለ የሕግ ማዕቀፍ እና ሥርዓት መመራት ያለባቸው በመሆኑ ይኸው ድንጋጌ በረቂቅ አዋጁም ተጠብቆ እንዲቀጥል ተደርጓል፡፡ ማዕድን እና ነዳጅ ከተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶች ሊገኙ የሚችሉ በመሆኑ ምን ዓይነት የተፈጥሮ ሀብት ማዕድን ወይም ነዳጅ እንደሆነ የሚወሰነው አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ ይሆናል፡፡

- <u>አንቀጽ 4 - የሥልጣን ክልል</u>፡

በአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፣ በኤሌክትሪክ ማመንጨት፣ ማስተላለፍ ወይም ማሰራጨት አገልግሎት፣ በኮሙኒኬሽን እና በፋይናንስ አገልግሎት የሚደረግ ኢንቨስትመንት አስተዳደር በኢንቨስትመንት ሕግ የሚገዛ ቢሆንም በመስኮቹ የሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶች ሊፈቀዱ እና ሊከናወኑ ከሚችሉበት ልዩ ሁኔታ አንጻር የኢንቨስትመንት ፈቃድ እና ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶች መስኮቹ ላይ ልዩ ዕውቀት ባላቸው እና አስፈላጊውን ዝግጅት ባደረጉት በቅደም ተከተል የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን፤ የኢትዮጵያ በኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የሚሰጡ በመሆኑ፤ እነዚህ ተቋማት በረቂቅ አዋጁ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመተግበር የሚያስችሏቸውን የአፈጻጸም መመሪያዎች ከኮሚሽኑ ጋር በመመካከር የማውጣት ሥልጣን በረቂቅ አዋጁ በግልጽ እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡ እነዚህ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ በሚሰጡባቸው መስኮች ያሉ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን እና ሀብቶችን ለመለየት የሚያስፈልጉ ጥናቶችን የማካሄድ፣ የየመስኮቹን የልማት ስትራቴጂዎች የመቅረጽ እንዲሁም በዘርፎቹ ያሉ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን የማስተዋወቅ ሥራዎችን ከኮሚሽኑ ጋር በመቀናጀት የሚያከናውኑ ይሆናል፡፡

### 2.2.3 ክፍል ሦስት - የኢንቨስትመንት መስኮች፣ የድርጅት ዓይነቶች እና የካፒታል መጠን

- አንቀጽ 6 - ባለሀብቶች ሊሰማሩ የሚችሉባቸው የኢንቨስትመንት መስኮች፡
  - ✓ አንቀጽ 6/1/፦ አገሪቱ ውስጥ የሚካሄዱ ማናቸውም ኢንቨስትመንቶች ለሕግ፣ ለሞራል፣ ለማህበረሰብ ጤና ወይም ደህንነት የማይቃረኑ መሆን ያለባቸው በመሆኑ ይህንን የሚያመለክት ድንጋጌ ተካቷል። ይህ ድንጋጌ የተካተተው በግልጽ ያልተከለከሉ ነገር ግን የተለያዩ ማህበረሰቦችን ሞራል የሚቃረኑ ወይም ጤና እና ደህንነት የሚያውኩ ‹‹እንቅስቃሴዎችን›› ለመከላከል ነው።
  - ✓ አንቀጽ 6/2/፣ 6/3/ እና 6/4/፦ ለባለሀብቶች የተከለሉም ሆነ ክፍት የተደረጉ የኢንቨስትመንት መስኮችን በሕግ በተፈቀደ አግባብ ነባራዊ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ባገናዘበ ሁኔታ በየጊዜው መከለስ አስፈላጊ ሊሆን የሚችል በመሆኑ ባለሀብቶች ሊሰማሩ የሚችሉባቸው ሁሉም የኢንቨስትመንት መስኮች በደንቡ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የግሉ ሴክተር በአገሪቱ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ብሎም ኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ሚና ለማሳደግ፣ በመንግሥት የተያዙ ድርጅቶችን በከፊል ለግሉ ሴክተር በሽያጭ በማስተላለፍ እና እነዚህ ድርጅቶች የተሰማሩባቸውን እንዲሁም ሌሎች ለግል ሴክተር ወይም ለውጭ ባለሀብቶች ዝግ የሆኑ ዘርፎችን ክፍት በማድረግ የነጻ ኢኮኖሚ ፖሊሲውን በአግባቡ ለመተግበር፣ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ሕጉን ከአፍሪካ አህጉራዊ የነጻ-ንግድ ቀጠና ግዴታዎች እና ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ከምታደርገው ጥረት ጋር በተናበበ ሁኔታ በሥራ ላይ ያለውን ለኢንቨስትመንት ክፍት የተደረጉ የሥራ መስኮች ማሻሻል በማስፈለጉ ረቂቅ ሕጉ ለኢንቨስትመንት ክፍት የተደረጉ የሥራ መስኮች የተዘረዘሩበትን መንገድ የሚለውጥ ድንጋጌ አካቷል። በዚህም መሠረት፤ ረቂቅ አዋጁ በረቂቅ ደንቡ የሚዘረዘረው ከመንግሥት ወይም ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር በጋራ የሚካሄዱ እንዲሁም ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ የኢንቨስትመንት መስኮች ብቻ እንደሚሆኑ እና ከዚህ ውጭ ያሉ የኢንቨስትመንት መስኮች በሙሉ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት እንደሚሆኑ ይደነግጋል። ሆኖም፤ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ቀደም ሲል የነበረው የኢንቨስትመንት መስኮችን የመከለል እና የመክፈት ሥልጣን የተጠበቀ ይሆናል።

- አንቀጽ 8 - የኢንቨስትመንት ሥራዎች የሚካሄድባቸው ድርጅቶች ዓይነት፡

  አንቀጽ 8/3/፦ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ውጭ አገር በተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች ሊካሄዱ ይችላሉ። ሆኖም፤ የንግድ ድርጅቶቹ የተቋቋሙት ውጭ አገር ቢሆንም የኢንቨስትመንት ሥራ ማከናወን የሚችሉት የንግድ ሕጉን ጨምሮ ተፈጻሚነት ባላቸው የኢትዮጵያ ሕጎች መሠረት ብቻ በመሆኑ ይህን የሚያመለክት ድንጋጌ ተካቷል። ይህ ድንጋጌ ያስፈለገው ውጭ አገር የተቋቋመ ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሕግ እና አሠራር

በቀጥታ ሊፈጸምበት አይችልም በሚል ዕሳቤ በሕግ ከተመለከተው አሠራር ውጭ እንዳይሆን ለማድረግ ነው።

- <u>አንቀጽ 9 - ከውጭ ባለሀብት የሚጠየቅ ዝቅተኛ የካፒታል መጠን</u>፡

  የውጭ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ሥራ ላይ ለመሠማራት እንዲመድቡ የሚጠየቀው ዝቅተኛ የካፒታል መጠን ላይ ለውጥ ሳይደረግ ከጉዳዩ እና ከሥራው ልዩ ባህርይ የተነሳ ዝቅተኛ የካፒታል መጠን መመደብ አስፈላጊ የማይሆንባቸው ሁለት ተጨማሪ ሁኔታዎች (ሌላው ልዩ ሁኔታ ከነባር ኢንቨስትመንት በተገኘ ትርፍ የሚከናወን ኢንቨስትመንት ሆኖ) እንዲለዩ ተደርጓል።

  ✓ አንቀጽ 9/4/ለ/፦ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወደ አክስዮን ማኅበር ሲቀየር አክስዮን ማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሊኖረው የሚገባ በመሆኑ እና የቦርዱ አባላት ደግሞ የማኅበሩ አባላት መሆን ያለባቸው በመሆኑ፤ ማኅበሩ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሆኖ ሲቋቋም ዝቅተኛውን የካፒታል መጠን ስላሟላ የአክስዮን ማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የሚሆኑ ግለሰቦች ብቻ ዝቅተኛ የካፒታል መጠን የመመደብ ግዴታ እንዳይኖርባቸው ተደርጓል።

  ✓ አንቀጽ 9/4/ሐ/፦ የውጭ ባለሀብት ከውጭ ባለሀብቶች የሚጠበቀውን ዝቅተኛ ካፒታል መድቦ ሲሰራ ከነበረ የውጭ ባለሀብት ሙሉ ድርጅቱን ወይም የንግድ ማህበር ከሆነ የሻጩን የውጭ ባለሀብት ድርሻ ሲገዛ ግዢውን በድርጅቱ ወይም በድርሻው የገበያ ዋጋ ልክ መፈጸም እንዲችል ዝቅተኛ የካፒታል መጠን የመመደብ ግዴታ እንዳይኖር ተደርጓል።

### 2.2.4 ክፍል አራት - የኢንቨስትመንት ፈቃድ

- <u>አንቀጽ 11 - የኢንቨስትመንት ፈቃድ ዕድሳት</u>

  ✓ አንቀጽ 11/3/ እና አንቀጽ 11/5/፦ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሰዱበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ የኢንቨስትመንት ትግበራ (ለምሳሌ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ ቦታ ዝግጅት) መጀመር አለባቸው፤ የትግበራ ሥራውን የሚያጠናቅቁበት ጊዜም መታወቅ አለበት። ፈቃዱ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ትግበራው ለሁለት ዓመት ካልተጀመረ ወይም ይጠናቀቃል ከተባለበት ጊዜ በሁለት ዓመት ከዘገየ ፈቃዱ የማይታደስ በመሆኑ ይሰረዛል። ፈቃዱ ሊታደስ የሚችለው ትግበራው ያልተጀመረው ወይም ያልተጠናቀቀው በበቂ ምክንያት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል።

### 2.2.5 ክፍል ስድስት - የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች፣ ዋስትና እና ጥበቃ፣ እና ማሳለጥ

- <u>አንቀጽ 17 - የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች</u>፡

ከላይ እንደተመለከተው ረቂቅ አዋጁም ሆነ ደንቡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ የማይደነግጉ በመሆኑ ማበረታቻ የሚያገኙ የኢንቨስትመንት መስኮች እንዲሁም የማበረታቻዎች ዓይነት እና መጠን የሚወስን ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወጣ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡

- <u>አንቀጽ 18 - የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት</u>

የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ የውጭ ዜጎች ኢትዮጵያ ውስጥ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት ከመሆን የሚገድብ ቢሆንም በኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ የውጭ ዜጎች ግን ሥራቸውን ለማካሄድ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሊያስፈልጋቸው የሚችል በመሆኑ ሁሉም የውጭ ባለሀብቶች ለሥራቸው የሚያስፈልጋቸውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት መሆን እንዲችሉ፤ እንዲሁም ከፍተኛ መጠን ያለው ኢንቨስትመንት ያላቸው ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ አንድ የመኖሪያ ቤት እንዲኖራቸው የሚፈቅድ ድንጋጌ ተካቷል፡፡ ለመኖሪያ የሚሆን ቤት ባለቤት ለመሆን ከፍተኛ መጠን ያለው ኢንቨስትመንት መጠየቁ የውጭ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንታቸውን እንዲያስፋፉ እንደሚያበረታታ ታምኖበታል፡፡ መኖሪያ ቤትን የተመለከተውን ድንጋጌ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር ሁኔታዎች በደንብ የሚወሰኑ ይሆናል፡፡

- <u>አንቀጽ 20 - ገንዘብ ወደ ውጭ አገር ማዛወር</u>፡

አንቀጽ 2/3/፦ በረቂቅ አዋጁ መሠረት ለሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶች የሚያስፈልጉ ቋሚ ነዋሪነታቸው ውጭ አገርም ሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የውጭ አገር ዜጎች በአዋጁ እና በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ሊቀጠሩ ይችላሉ፡፡ ሆኖም፤ ከቅጥራቸው የሚያገኙትን ገንዘብ ወደ ውጭ አገር መላክ ወይም ማውጣት የሚችሉት ግን ቋሚ ነዋሪነታቸው ከኢትዮጵያ ውጭ የሆነ የውጭ አገር ዜጎች ብቻ እንደሆኑ ተደንግጓል፡፡

- <u>አንቀጽ 22 - የውጭ ዜጎች ቅጥር እና የሥራ ፈቃድ</u>፡
  - ✓ አንቀጽ 22/1/ - 22/3/፦ ከኢንቨስትመንት ዓላማዎች መካከል አንደኛው ለዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር በመሆኑ በኢንቨስትመንት ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች ኢትዮጵያውያንን እንዲቀጥሩ ይጠበቃል፡፡ ሆኖም፤ አስፈላጊው የትምህርት ዝግጅት፣ ልምድ እና ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ካልተገኙ በተቆጣጣሪነት፣ በአሰልጣኝነት እና በሌሎች የቴክኒክ ሥራዎች ላይ የሚሰማሩ የውጭ አገር ዜጎችን መቅጠር እንዲችሉ፤ እንዲሁም ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ የኦፐሬሽን ኃላፊ እና የፋይናንስ ኃላፊን ጨምሮ ከፍተኛ የማኔጅመንት አባላት የሆኑ የውጭ ዜጎችን እንደ አስፈላጊነቱ መቅጠር እንዲችሉ ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም፤ የባለሀብት እንዲሁም በአዋጁ መሠረት የሥራ ፈቃድ የተሰጠው/ጣት የውጭ ዜጋ የትዳር አጋር የሥራ ፈቃድ ሊሰጣት/ጠው የሚችል ስለመሆኑ ያስቀምጣል፡፡

- ✓ አንቀጽ 22/4/፦ ከከፍተኛ የማኔጅመንት ሥራዎች ውጭ ያሉ የሙያ ወይም የቴክኒክ የሥራ መደቦች ላይ የተቀጠሩ የውጭ ዜጎች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያውያን የመተካት፤ ይህን ለመፈጸም ደግሞ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞችን በመመልመል የማሰልጠን ግዴታ እንዲኖር ተደርጓል። ይህን ኢትዮጵያውያንን የማሰልጠን ግዴታ ተፈጻሚነት ለማረጋገጥም ለውጭ ዜጎች የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ ዕድሳት ከማሰልጠን ጋር በተያያዘ ከተከናወኑ ተጨባጭ ሥራዎች ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል።

- <u>አንቀጽ 23 - የቪዛ አገልግሎት</u>፡

  ረቂቅ አዋጁ ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት ለመሰማራት ወይም ኢንቨስትመንታቸውን ለመከታተል ወደ ኢትዮጵያ የሚያደርጉት ጉዞ ለማቅለል የተለያዩ የቪዛ አገልግሎት እዲያገኙ የሚያስችል ድንጋጌ አካቷል። በዚህም መሠረት፤ ለኢንቨስትመንት ጉዳይ ወደ ኢትዮጵያ ለመንዝ ከሦስተኛ አገር ሆኖ ቪዛ መጠየቅን የሚፈቅድ ሲሆን፣ የኢንቨስትመንት ባለቤት ወይም ባለድርሻ የአምስት አመት የብዙ ጊዜ መመላለሻ የኢንቨስትመንት ቪዛ እንዲሁም ሥራ አስኪያጆች፣ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች እና ሌሎች ከፍተኛ የማኔጅመንት ቦታ ያላቸው የውጭ ዜጎች የሦስት ዓመት የብዙ ጊዜ መመላለሻ የኢንቨስትመንት ቪዛ ሊያገኙ የሚችሉበትን አግባብ የሚያስቀምጥ ድንጋጌ ተካቷል።

- <u>አንቀጽ 24 - የአንድ ማዕከል አገልግሎት</u>፡

  አንቀጽ 24/2/፦ የአንድ ማዕከል አገልግሎት በኢንቨስትመንት መስክ ለተሰማሩ ሁሉም ባለሀብቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ እና በዝቅተኛ ወጪ የተቀናጀ እና ወጥ የሆነ አገልግሎት በመስጠት ኢንቨስትመንቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ማስቻል በመሆኑ በክልል የኢንቨስትመንት አካላት የሚስተናገዱ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችም ተመሳሳይ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል ድንጋጌ ተካቷል።

### 2.2.6 ክፍል ሰባት - የአቤቱታ ሥርዓት እና የኢንቨስትመንት አለመግባባት አፈታት

- <u>አንቀጽ 25 - አቤቱታ የማቅረብ መብት</u>፡

  ኢንቨስትመንትን የተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ቅሬታ ሊኖር የሚችለው ኢንቨስትመንት የሚካሄድበት ድርጅት ከተቋቋመ በኋላ ከሚኖሩ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ብቻ ባለመሆኑ የቅሬታ ማስተናገጃ ሥርዓቱ ወደ ኢንቨስትመንት ለመግባት ከሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችንም የሚመለከት ስለመሆኑ ረቂቅ አዋጁ ይደነግጋል።

- <u>አንቀጽ 26 - የኮሚሽኑ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ</u>፡

  - ✓ አንቀጽ 26/4/፦ ባለሀብቶች በኮሚሽኑ የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔን በተመለከተ ለቦርዱ ቅሬታ ማቅረብ እንደሚችሉ በሥራ ላይ ያለው ሕግም የሚደነግግ ቢሆንም ቦርዱ ውሳኔ

ስለሚሰጥበት ጊዜ ግን የማያመለክት በመሆኑ ይህን ክፍተት ለማስተካከል ለቦርዱ የሚቀርብ ቅሬታ በ 90 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ እንደሚያገኝ ረቂቅ አዋጁ ይደነግጋል፡፡

- አንቀጽ 27 - ከኮሚሽኑ ውጭ ባሉ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት የሚሰጥ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ፡

በአዋጁ መሰረት የሚካሄድ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ በፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት የመጨረሻ ውሳኔ ከተላለፈ እና ውሳኔው ኢንቨስትመንቱ ላይ ጉልህ የሆነ ተጽዕኖ የሚኖረው ከሆነ ለኮሚሽኑ ቅሬታ ማቅረብ የሚያስችል ድንጋጌ ተካቷል፡፡ የኮሚሽኑ ኃላፊነት ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር በ 30 የሥራ ቀናት ውስጥ የመፍትሔ ሀሳብ ማቅረብ እንደሚሆን፣ ባለሀብቱ በመፍትሔ ሀሳቡ ካልተስማማ ለኢንቨስትመንት ቦርድ በ 30 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታ ማቅረብ እንደሚችል፣ ቦርዱ በ 90 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ እንደሚሰጥ እንዲሁም የሚመለከተው አካል የቦርዱን ውሳኔ የመፈጸም ግዴታ እንዳለበት የሚያስቀምጡ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡ በተጨማሪም፤ አቤቱታ የማቅረብ መብቱ ወደ ኢንቨስትመንት ለመግባት በሚደረጉ ጥረቶች ወቅት በሚያጋጥሙ ጉዳዮች ላይ የተመሰረቱ ቅሬታዎችንም የሚመለከት ይሆናል፡፡

- አንቀጽ 28 - የኢንቨስትመንት አለመግባባት አፈታት፡

ለረቂቅ የኢንቨስትመንት ሕጉ ዓላማ የኢንቨስትመንት አለመግባባት ማለት በኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት ወይም በሌሎች መንግሥታዊ አካላት የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ የተላለፈበት መንግሥት እና ባለሀብት ያልተስማሙበት ጉዳይ ማለት ነው፡፡ በሥራ ላይ ያለው አዋጅ የኢንቨስትመንት አለመግባባት የሚፈታበትን አግባብ አይደነግግም፡፡ የዚህ ዓይነት ድንጋጌ መኖር ባለሀብቶች በኢንቨስትመንት አስተዳደር ሕጉ የበለጠ ዕምነት እንዲኖራቸው የሚያስችል በመሆኑ በረቂቅ አዋጁ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት፦

- ✓ አንቀጽ 28/1/፣ 28/2/፣ 28/3/፦ በመንግሥት እና በባለሀብቶች መካከል የሚነሳ ማንኛውንም የኢንቨስትመንት አለመግባባት መፍታት የሚፈለገው ኢንቨስትመንትን በሚያስቀጥል፣ ከባለሀብቶች ጋር የሚኖር መልካም ግንኙነትን በሚጠብቅ እና ጊዜ እና ወጪን በሚያድን አግባብ በመሆኑ የመጀመሪያው ምርጫ አለመግባባቱን በውይይት እና ድርድር ለመፍታት መሞከር እንደሚሆን፣ ይህ ጥረት በስድስት ወራት ውስጥ ውጤታማ ካልሆነ ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከውጭ ባለሀብት ጋር የሚነሳ የኢንቨስትመንት አለመግባባትን በተመለከተ የግልግል ዳኝነት እንዲካሄድ የፌደራል መንግሥት በልዩ ሁኔታ ሊፈቅድ የሚችልበት አግባብም ተደንግጓል፡፡ የግልግል ዳኝነቱ

በመንግሥት እና በባለሀብት ወይም በመንግሥት እና ባለሀብቱ ዜጋ በሆነበት ወይም በተመዘገበበት/በተቋቋመበት አገር መካከል እንዲካሄድ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

✓ አንቀጽ 27/4/፦ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 27/2/ እና 27/3/ መሠረት የውጭ ባለሀብቶች ሊኖራቸው የሚችል የኢንቨስትመንት አለመግባባትን በፍርድ ቤት ወይም በግልግል ዳኝነት እንዲፈታላቸው የመጠየቅ መብት ያላቸው በመሆኑ ምርጫ ውስጥ እንዳይገቡ ለመከላከል ከሁለቱ አንዱን መርጠው ጉዳዩ በፍርድ ቤት ወይም በግልግል ጉባዔ መታየት ከጀመረ በኋላ በሌላኛው አካል እንዲታይ መጠየቅ የሚከለክል ድንጋጌ ተካቷል፡፡

### 2.2.7 **ክፍል ስምንት- የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት**

- <u>አንቀጽ 29 - የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት</u>፡

  የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችን እና የአፈጻጸም ሀሳቦችን መቅረጽ እና መተግበር ጨምሮ ኢንቨስትመንት የማበረታታት፣ የማስተባበር፣ የማስፋፋት፣ የመመልመል፣ የመቀበል፣ የመፍቀድ፣ የመመዝገብ፣ ኢንቨስትመንትን የተመለከቱ ቅሬታዎች የመፍታት እንዲሁም ሌሎች ኢንቨስትመንትን የሚመለከቱ ተግባራትን የሚያከናውኑ አካላት ማቋቋም ውጤታማ የኢንቨስትመንት አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖር ስለሚያግዝ በየደረጃው የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት ተቋቁመው አገልግሎት ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡ እነዚህም፤ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እና የክልል ኢንቨስትመንት አካላት ናቸው፡፡ እነዚህ እንደተጠበቁ ሆኖ፤ ከቀን ተቀን ሥራዎች ጋር በተያያዘ ከሚነሱ ጉዳዮች የተለዩ በአገሪቱ የሚካሄዱ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን አጠቃላይ አቅጣጫ ሊወስኑ የሚችሉ የተለያዩ የፌደራል እና የክልል አካላትን የጋራ ምክክር እና አመራር የሚጠይቁ በወቅታዊ ሁኔታዎችም ሆነ በሌሎች ምክንያቶች የሚከሰቱ ከፍተኛ ጉዳዮችን የሚመለከት አካል ማቋቋም አስፈላጊ እንደሆነ ስለታመነ ረቂቅ አዋጁ *"የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድሮች የኢንቨስትመንት ጉባዔ"* የሚባል አካል ያቋቁማል፡፡

- <u>አንቀጽ 30 - 43፦ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ እና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን</u> ፡

  በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 313/2006 የተቋቋሙት የኢንቨስትመንት ቦርድ እና የኢንቨስትመንት ኮሚሽን በተቋቋሙበት ደንብ፣ በአዋጅ ቁጥር 769/2004 እና በደንብ ቁጥር 270/2005 የተዘረዘሩ ሥልጣን እና ተግባራት እንዲኖራቸው ተደርጎ በድጋሚ በረቂቅ አዋጁ የሚቋቋሙ ይሆናል፡፡ የኢንቨስትመንት ቦርድን በተመለከተ፤ የቦርዱ አባላት ቁጥር አስራ ሶስት እንዲሆን፣ የኮሚሽኑን ጨምሮ ከኢንቨስትመንት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ካላቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎች በተጨማሪ አሳታፊነትን ለማረጋገጥ የውሳኔ ድምጽ የማይኖራቸው ሁለት የግሉን ዘርፍ የሚወክሉ ሰዎች የቦርዱ አባላት እንዲሆኑ ረቂቅ አዋጁ ይደነግጋል፡፡

ከቦርዱ አሠራር ጋር በተያያዘ እንደ ችግር የሚጠቀሰው በየጊዜው መሰብሰብ አለመቻሉ በመሆኑም ተገማች የሆነ አሠራር እንዲኖር በሦስት ወራት አንድ ጊዜ የሚሰበሰብ ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡

የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች የሚወሰኑት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ስመሆኑ ረቂቅ አዋጁ ስለሚደነግግ ማበረታቻ ሊሰጣቸው የሚገባ የኢንቨስትመንት መስኮችን እንዲሁም የማበረታቻውን ዓይነት እና መጠን ለመወሰን የሚያግዝ መሥፈርት ወይም መመዘኛ በጥናት የመለየት ኃላፊነት የቦርዱ እንደሚሆን ተደንግግል (አንቀጽ 31(1)(ሰ)፡፡ ቦርዱ ለኢንቨስትመንት ክፍት የተደረጉ መስኮች ላይ ለውጥ ማድረግ የሚችል ስለመሆኑ ረቂቅ አዋጁ የሚደነግግ በመሆኑ ይህን ዓይነት ለውጥ የሚያስከትል ውሳኔ ተፈጻሚ የሚሆነው ወዲያው እንደሚሆን፤ ሆኖም ተደራሽነትን ለማረጋገጥ በአንድ ወር ውስጥ በወረቀት ህትመት ወይም በሌላ መንገድ ለሕዝብ ማሳወቅ እንደሚኖርበት ተደንግጓል (አንቀጽ 31(2))፡፡

- <u>አንቀጽ 34 - የኢንቨስትመንት አማካሪ ኮሚቴ፡</u>

  ኢንቨስትመንትን የተመለከቱ ፖሊሲዎችን መቅረጽ እና ተግባራዊ ማድረግ የተለያዩ ዘርፎች ላይ ጥልቅ ዕውቀት እና ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑ ሥራውን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማከናወን እንዲቻል ቦርዱ የኢንቨስትመንት አማካሪ ኮሚቴዎች ማቋቋም የሚችል ስለመሆኑ ረቂቅ አዋጁ ይደነግጋል፡፡

- <u>አንቀጽ 44 - 49፦ የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድሮቸ የኢንቨስትመንት ጉባዔ (ጉባዔ)፡</u>

  የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳደሮቸ የኢንቨስትመንት ጉባዔ (ጉባዔ) በረቂቅ አዋጁ አዲስ የሚቋቋም የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካል ሲሆን ያስፈለገበት ምክንያትም በአገራዊ ደረጃ ለሚያጋጥሙ የኢንቨስትመንት ተግዳሮቶች መፍትሔ በማበጀት የተቀናጀ እና ወጥ የሆነ የኢንቨስትመንት አስተዳደር ሥርዓት እንዲኖር መርዳት ይሆናል፡፡ ይህን ዓላማውን በፌደራል እና በክልል አስተዳደሮች መካከል የሚኖር የጎንዮሽ ግንኙነቶችን በበላይነት በመምራት፣ ለባለሀብቶች የሚሰጡ ቅድመ- እና ድህረ-ኢንቨስትመንት አገልግሎቶችን አስመልክቶ የሚነሱ መሠረታዊ ወይም ጉልህ አለመግባባቶችን የተመለከተ ውሳኔ በመስጠት እና ሌሎች በረቂቅ አዋጁ በግልጽ የተመለከቱ ተግባራትን እንዲያከናውን ተደንግጓል፡፡ ጉባዔው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት የሚመራ፣ የሁሉም ክልሎች ርዕሰ-መስተዳድሮች እና የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች ከንቲባዎች፣ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር፣ የክልሎቹ እና የከተሞቹ ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ኃላፊዎች እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሰዎች አባላት የሚሆኑበት አካል እንዲሆንም

ረቂቅ አዋጁ ይደነግጋል:: ከላይ እንደተመለከተው የጉባዔው ዓላማ በቀን ተቀን ሥራዎች የሚያጋጥሙ የኢንቨስትመንት ጉዳዮችን እንዲመለከት ሳይሆን መሠረታዊ የሆኑ ችግሮችን መፍታት እና አቅጣጫዎችን ማመላከት በመሆኑ በስድስት ወራት አንድ ጊዜ እንዲሰበሰብ፤ ሆኖም አስቸኳይ ጉዳይ ሲገጥም በማናቸውም ጊዜ እንዲሰበሰብ እና ውሳኔ ወይም የመፍትሔ ሀሳብ እንዲያሳልፍ ይደነግጋል:: ማናቸውም የፌደራል መንግሥት እና እና የክልል መንግሥት አካላት የጉባዔውን ውሳኔዎች እና የመፍትሔ ሀሳቦች የመፈጸም ግዴታ እንደሚኖርባቸውም ረቂቅ አዋጁ ይደነግጋል::

- <u>አንቀጽ 50/3/ - በክልል ሕጎች ከሚመሠረቱ የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት ጋር ስለሚኖር ቅንጅት</u>

  በአገሪቱ የሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶች የሚፈለገውን ውጤት ሊያስገኙ የሚችሉት ኢንቨስትመንቶቹ በሚካሄዱባቸው ክልሎች በሚገኙ ሀብቶች እና የኢንቨስትመንት ዕድሎች ላይ ተመሥርተው ሲከናወኑ፣ የክልል አስተዳደሮች ለኢንቨስትመንቶች ሙሉ ድጋፍ ማድረግ ሲችሉ እና የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታት ሲችሉ በመሆኑ ይህን ሥራ ከኮሚሽኑ ሥራ ጋር ለማቀናጀት በኮሚሽኑ ተቋማዊ መዋቅር ውስጥ ቋሚ የክልል ኢንቨስትመንት አስተዳደር ዴስክ ማቋቋም የሚያስችል ድንጋጌ ተካቷል::

- <u>አንቀጽ 51 - የኢንቨስትመንት መሬት አቅርቦትን በተመለከተ ስለሚጸሙ አሰራሮች</u>፡

  ለኢንቨስትመንት ከሚያስፈልጉ መሠረታዊ ግብዓቶች መካከል ዋነኛው መሬት በመሆኑ የመሬት አቅርቦት ሥርዓቱ ቀልጣፋ፣ ግልጽ እና ተገማች መሆን አለበት:: ይህን ለማድረግም፤ ክልሎች በሕግ በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት ለኢንቨስትመንት የሚውል መሬትን አስቀድሞ በመለየት በአንድ የክልል ተጠሪ አካል ሥር አድርገው መረጃውን ለሚመለከታቸው የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት እንዲልኩ፤ እንዲሁም በባለሀብቶች የመሬት ጥያቄ ሲቀርብ ለማምረቻ ዘርፍ ኢንቨስትመንት በ 60 ቀናት፣ በሌሎች ዘርፎች ለሚካሄድ ኢንቨስትመንት ደግሞ በ 90 ቀናት ውስጥ ምላሽ እንዲሰጥ የሚያስችል አሠራር እንዲዘረጉ የሚያደርግ ድንጋጌ ተካቷል::

### 2.2.8 ክፍል ዘጠኝ - ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

<u>አንቀጽ 53 - ሌሎች ሕጎችን የማክበር እና ዘላቂ የማህበራዊ እና የአካባቢ ጉዳዮች ግዴታ</u>፡

ባለሀብቶች ኢንቨስትመንታቸውን ተፈጻሚነት ባላቸው የአገሪቱ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የማህበራዊ እና አካባቢያዊ ደህንነትን እና ዕሴቶችን በተለይም የአካባቢ ጥበቃ እና ማህበራዊ አካታችነት ዓላማዎችን ለማሳካት በሚያስችል አግባብ ማከናወን እንዳለባቸው ረቂቅ አዋጁ ይደነግጋል:: ይህም፤ በአገሪቱ የሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶች በሕግ ከተደነገጉ ግዴታዎቻቸው

በተጨማሪ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶቻቸው ለሚገኙባቸው አካባቢዎች እና ለአገሪቱ በአጠቃላይ ማህበራዊ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን መሠረት በማድረግ የተካተተ ድንጋጌ ነው፡፡

<u>አንቀጽ 56 - የመሸጋገሪያ ድንጋጌ፡</u>

በዚህ ማብራሪያ መግቢያ ላይ እንደተመለከተው፤ ረቂቅ አዋጁ የተዘጋጀበት መሠረታዊ ዓላማ ከወቅታዊ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር የሚሄድ ቀልጣፋ እና ተወዳዳሪ የኢንቨስትመት ከባቢ በመገንባት በመጠን እና በጥራት የተሻለ የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲኖር እና የተቋቋሙ ኢንቨስትመንቶችም እንዲስፋፉ በማድረግ በአገሪቷ ውስጥ ከሚካሄዱ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች ሊገኝ የሚችለውን አገራዊ ጥቅም ማሳደግ ነው፡፡ የኢንቨስትመንት ከባቢውን ለኢንቨስትመንቶች የበለጠ ተስማሚ ማድረግ ከሚቻልባቸው መንገዶች ዋነኛው ሥራ ላይ ካሉት ተጨማሪ የሆኑ ጠቃሚ አሠራሮችን፣ መብቶችን እና ጥቅሞችን ማካተት ቢሆንም ነባር አሠራሮች፣ መብቶች እና ጥቅሞች እንዲቀጥሉ ማድረግም ተመሳሳይ ዋጋ ያለው ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም፤ ረቂቅ አዋጁ ጸድቆ ሥራ ላይ ከሚውልበት ጊዜ በፊት በነባር የኢንቨስትመንት ሕጉ መሠረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚሰጣቸው ኢንቨስትመንቶች በዚያ ሕግ መሠረት የሚያገኙት ጥቅም የሚቀጥል ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

***